## በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ



በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# ከሴፕቴምበር 1-10፣ የነበረው የአየር ሁኔታ እና

# ከሴፕቴምበር 11-20፣ ከሴፕቴምበር 21-30/2026 የሚኖረዉ የአየር

# ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ሴፕቴምበር 2026

አዲስ አበባ

## 1. እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፉት አስር ቀናት በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን፣ መካከለኛዉ እና ሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን ነበራቸዉ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ እና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል፡፡ በአጠቃላይ ባለፉት አስራ አንድ ቀናት በ29 የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ30-76.6 ሚ.ሜ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ ነበራቸዉ (ምስል 1) ፡፡

ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካከል አዲስ አበባ ጥቁር አንበሳ 40.2፣ አድዋ 41.2፣ አይራ 76.6፣ ቢላምቢሎ 57፣ ጨፋ 42.1፣ ዳንግላ 47.5፣ ኢጃጂ 50.5፣ ቁሉቢ 42.6፣ ማሻ 60፣ ነቀምት 45.6፣ ሮቢት 41.3፣ ሻምቡ 44.3፣ ተርጫ 53.5፣ ወራቤ 42.1፣ ይትኖራ 71 ይገኙበታል ፡፡




ምስል1:ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2026 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ሸገር ከተማ፣ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉና ደቡብ ጎንደር፣ ባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ አዊ፣ የደቡብ እና የሰሜን ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ እና መካከለኛዉ፣ ትግራይ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ልዩ ወረዳ፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ሸካ፣ ቤንች ሸኮ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳዉሮ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ሀዲያ፣ የም፣ ስልጤ፣ ሃላባ፣ ከምባታ ዞኖች፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ፤ እና አዲስ አበባ ላይ ከ21-160 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ3-10 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር፤ ከኦሮሚያ ክልል ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ሸገር ከተማ፣ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉና ደቡብ ጎንደር፣ ባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ አዊ፣ የደቡብ እና የሰሜን ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የምዕራብ እና የሰሜን ምዕራብ ትግራይ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ልዩ ወረዳ፣ ከጋምቤላ ክልል አኙዋክ፣ መዥንግ፣ ኑዌር እና ኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ አዲስ አበባ በአብዛኛው መደበኛ እና በጥቂት ቦታዎቻቸዉ ላይ ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2026 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2026 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2026 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር

## 1.2 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት የሴፕቴምበር የመጀመሪያ አስር ቀናት የክረምት ዝናብ ተጠቃሚና የመኸር አብቃይ የሆኑት አብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ ነበር፡፡ ይህም የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ቀደም ሲል ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃና ፍሬ በመሙላት ላይ ለሚኙት እንደ ማሽላና በቆሎ ለመሳሰሉት የረጅም ጊዜ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች፣ ለፍራፍሬዎችና ለጓሮ አትክልቶች የውሃ ፍላጎታቸውን ከመሟላት አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ በተጨማሪም የክረምት ወቅታቸውን ጠብቀው ተዘርተው ፍሬ በማፍራትና በማበብ ላይ ባሉት የመካከለኛና የአጭር ጊዜ ሰብሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ምቹ ሁኔታን ከመፍጠሩም በላይ በሰሜን ምስራቅና በምስራቅ ለሚገኙት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት ጠቀሜታው የጎላ ነበር (ካርታ 4)።

## 1.3 እ.ኤ.አ ከኦገስት ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2026 የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍናቸው የሴብቴምር የመጀመርያው አሥር ቀናት በአብዛኛው አባይ፣ ባሮ አኮቦ፣ ተከዜ፣ ላይኛውና መካከለኛ ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ላይኛውና መካከለኛ ዋቤ ሸበሌ እንዲሁም ላይኛው ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ በጣም ከፍተኛ የሆነ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ነበራቸው። እንዲሁም አይሻና ላይኛው ጥቂት ኦጋዴን ከመጠነኛ እስከ እርጥበታማ የገፀ ምድር ውኃ ፍሰት ነበራቸው። ይህ ሁኔታ ለገጸ ምድር፣ ለከርሰ ምድር፣ ለመስኖ፣ ለሃይል ማመንጫ እንዲሁም ለመጠጥ ውሃ አቅርቦትን መሻሻል አንጻር ከፍተኛ አስተዋፅዎ እንደነበራቸው የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ። በሌላ በኩል በአብዛኛው ኦጋዴን፣ አፋር ደናክል፣ መካከለኛና ታችኛው ዋቤ ሸበሌ፣ ገናሌ ዳዋ፣ አዋሽና ስምጥ ሸለቆ ተፋሰሶች ደረቅ ሁኔታ ስር ነበሩ (ካርታ 5)






## 2. እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11 እስከ 20/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ

በመጪዎቹ የሴፕቴምበር ሁለተኛው አሥር ቀናት ለዝናብ መፈጠር ምቹ ሁኔታን የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በደቡብ ምዕራብ እና ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች እየተስፋፉና እየተጠናከሩ ይሄዳሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በተለይም በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን፣ መካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የዝናብ መጠንና ሥርጭት እንደሚኖራቸው አሀዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 1)። ስለሆነም እርጥበታማው የአየር ሁኔታ በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና መካከለኛዉ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ በመጠንም ሆነ በሥርጭት እየተስፋፋ ከመሄዱ ጋር ተያይዞ በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም፣ በሰሜን ምስራቅ እና ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸዉ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 6 እና 7)፡፡ በሌላ በኩል በሰሜን ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ፣ መካከለኛው እና ምዕራብ  የሀገራችን አከባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት በረዶ የቀላቀለ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

በሚቀጥሉት አስር ቀናት ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ብዙ ቦታዎቻቸውን የሚሸፍን ሲሆን ከመካከለኛ እስከ ከባድ (ከ11-30 ሚ.ሜ) መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 7) ፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከሴፕቴምበር 11-20, 2026 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከሴፕቴምበር 11-20, 2026 የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን

ሠንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎችና በ24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን

| ክልል | ዞን | በ 24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን |
|---|---|---|
| ኦሮሚያ | ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፤ ጅማ ዞኖች እና ምዕራብ አርሲ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| | ምዕራብ አርሲ፣ ሸገር ሲቲ እና ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ሐረርጌ፣ ባሌ፣ ጉጂ እና የምዕራብ ጉጂ ዞን | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| አማራ | የምዕራብ፣ መካከለኛው፣ ደቡብ እና ሰሜን ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ የምዕራብ እና የምስራቅ ጎጃም፣ የሸዋ ዞኖች እና የአዊ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| | ዋግህምራ፣ የደቡብ እና ሰሜን ወሎ እና የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፤ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ጋምቤላ | አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ | ከቀላል እስከ መካካለኛ መጠን (ከ1 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| ቤንሻንጉል ጉምዝ | ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | ከፋ፣ ዳውሮ እና ሸካ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| | ኮንታ፣ ቤንች ሸኮ እና ምዕራብ ኦሞ | ከቀላል እስከ መካካለኛ መጠን (ከ1 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ እና ቀቤና ልዩ ወረዳ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |

| | | |
|---|---|---|
| | ሀዲያ፣ ከምባታ እና ማረቆ ልዩ ወረዳ | ከቀላል እስከ መካካለኛ መጠን (ከ1 እስከ 29 ሚ.ሜ በላይ) |
| አዲስ አበባ | | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ድሬዳዋ እና ሐረሪ | | ከቀላል እስከ መካካለኛ መጠን (ከ1 እስከ 29 ሚ.ሜ በላይ) |
| ትግራይ | የምዕራብ እና የሰሜን ምዕራብ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| | መካከለኛዉ፣ ምስራቅ፣ እና ደቡብ ትግራይ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| አፋር | የአዉሲ፣ ማሂ፣ ሀሪ እና ጋቢ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ሲዳማ ክልል | አብዛኛው የክልሉ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ እና ጌድዮ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ሶማሌ | ሲቲ እና ፋፈን ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |

Ethiopian Meteorology Institute

## 2.1 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በሚቀጥሉት የሴፕቴምበር ሶስተኛው አሥር ቀናት አሁን ከሚታዩትና በቀጣይነትም ከተተነበዩት የትንበያ መረጃዎች መረዳት እንደተቻለው ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ቀጣይነት ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም፤ በሰሜን ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ እንዲሁም መካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ በተጨማሪም የሰሜን ምስራቅ እና ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከሚጠናከሩ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ጋር ተያይዞ አልፎ አልፎ በሚኖሩ ቀናት ቀላል መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ። በሌላ በኩል በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ከቀን ወደ ቀን የደመና ሽፋን እየጨመረ እንደሚሄድ ከመጠበቁ ጋር ተያይዞ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 8) ፡፡




ካርታ 8 እ.ኤ.አ. ከሴፕቴምበር 21-30, 2026 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

Ethiopian Meteorology Institute

## 2.2 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11 እስከ 20/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት ቀናት በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና መካከለኛዉ የሀገራችን አካባቢዎች በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው የአፈር ውስጥ እርጥበት እንደሚኖር ይጠበቃል። እንድሁም በሰሜን ምስራቅ እና ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው የአፈር ዉስጥ እርጥበት ያገኛሉ። በመሆኑም የሚኖሩ መልካም አጋጣሚዎችን በአግባቡ ለመጠቀምና አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ለመቀነስ የሚያስችል ቦታ ተኮር የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳብ ከወዲሁ ተግባራዊ እንዲያደርጉ ከታች የቀረቡትን ዝርዝር ተግባራት ማከናነወን ያስፈልጋል (ሠንጠረዥ 2)፡፡

## 2.3 እ.አ.አ ከሴፕቴምበር 11 እስከ 20/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በውሀ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት ቀናት የክረምት ተጠቃሚ በሆኑ ተፋሰሶች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን የሚደረስ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ይኖራቸዋል። በመሆኑም የሚመለከታቸው የዘርፉ አካላት የሚኖሩ መልካም ዕድሎችን በአግባቡ ለመጠቀምና ተያያዥ ስጋቶችን ለመቀነስ የሚከተሉትን ተፋሰስ ተኮር የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል (ሠንጠረዥ 3)፡፡

Ethiopian Meteorology Institute

ሠንጠረዥ 2፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ

| የክረምት ዝናብ ተጠቃሚና የመኸር ሰብል አብቃይ እንዲሁም አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች | | | |
|---|---|---|---|
| **ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት የሚያገኙ ዞኖች** | **አዎንታዊ ተጽዕኖ** | **አሉታዊ ተጽዕኖ** | **የተሰጠ ምክረ ሃሳብ** |
| ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፤ ጅማ ፣ ምዕራብ አርሲ ፣ የምዕራብ፣ መካከለኛው፣ ደቡብ እና ሰሜን ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ የምዕራብ እና የምስራቅ ጎጃም፣ ሰሜን ሸዋ ፣ አዊ ፣ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ፣ ከፋ፣ ዳውሮ ፣ ሸካሞ፣ ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ ፣ አዲስ አበባ ፣ የመካከለኛዉ፣ ምስራቅ፣ እና ደቡብ ትግራይ ዞኖች ፡ ፡ | ➢ ለረጅምና መካከለኛ ጊዜ ሰብሎች እድገት እና ፍሬ ለማፍራት<br>➢ ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል<br>➢ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ የውሃ ማጠራቀሚያዎችን ለማጎልበት<br>➢ ለቋሚ ተክሎች እድገት እና ለግጦሽ ሳር ዕድገት<br>➢ ለአረንጓዴ እፅዋት ልምላሜ | ➢ የእርጥበት መብዛት እና ተዳፋታማ በሆኑ አካባቢዎች የውኃ በሰብሎች ላይ መተኛት<br>➢ ውሃገብ በሆኑና በወንዝ ዳርቻ ባሉ ሰብሎች ላይ የአፈር መታጠብ<br>➢ የአረም መስፋፋት<br>➢ የሰብል በሽታና ተባይ መከሰት<br>➢ የበረዶ ክስተት | ➢ ተዳፋታማ ማሳዎች ላይ የተዘጉ የማፋሰሻና የማንጣፈፊያ ቦዮችን ማስተካከል<br>➢ የሰብል በሽታንና አረምን አስቀድሞ መከላከል፤<br>➢ የአፈር መሸርሸር መከላከል ስራዎችን በስፋት መስራት<br>➢ እርጥበት አጠር አካባቢዎች የዝናብ ውሃን ማሰባሰብና ማጠራቀም<br>➢ አርሶ አደሮች የማሳ ጉብኝት በየጊዜው ማድረግ<br>➢ አረምን በወቅቱ ማረም፣ ፀረ-አረምና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ከግብርና ባለሙያ ጋር በመመካከር መተግበር<br>➢ አልፎ አልፎ የበረዶ ክስተት ስለሚኖር ጥንቃቄ ማድረግ |

| ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት የሚያገኙ ዞኖች | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የተሰጠ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|
| ምዕራብ አርሲ፣ ሸገር ሲቲ ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ሐረርጌ፣ ባሌ፣ ጉጂ ፣ የምዕራብ ጉጂ ፣ ዋግህምራ፣ የደቡብ እና ሰሜን ወሎ ፣ የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፣ አኘዋክ፣ መዠንግ፣ ኑዌር ፣ ኢታንግ ልዩ ወረዳ፣ ኮንታ፣ ቤንች ሸኮ ፣ ምዕራብ ኦሞ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ ፣ድሬዳዋ ፣ ሐረሪ ፣ የምዕራብ እና የሰሜን ምዕራብ ትግራይ፣ አዉሲ፣ ማሂ፣ ሀሪ ፣ ጋቢ ፣ የሲዳማ አብዛኛው የክልሉ ዞኖች፣ ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ ፣ ጌድዮ ፣ ሲቲ እና ፋፈን ዞኖች | ➢ ለረጅምና መካከለኛ ጊዜ ሰብሎች እድገት እና ፍሬ ለማፍራት<br>➢ የአረንጓዴ እፅዋት ልምላሜ፣ ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሣር አቅርቦት መሻሻል<br>➢ የዝናብ ውሃን ለማሰባሰብና ለማጠራቀም | ➢ የዝናብ መቆራረጥና ደረቅ ሰሞናት መኖር<br>➢ የትነት መጠን መጨመር፤<br>➢ የፀረ ሰብል ተባይ መከሰት ፤<br>➢ በተወሰኑ ቦታዎች ላይ የአፈር ውስጥ እርጥበት ዝቅተኛ መሆንና<br>➢ ለሰብሎች የውሃ ፍላጎት በቂ አለመሆን | ➢ የሚገኘዉን እርጥበት በአግባቡ መጠቀም<br>➢ የዝናብ ውኃን በማሰባሰብ በደረቅ ሰሞናት ተግባር ላይ ማዋል<br>➢ የአፈር ውስጥ የትነት መጠንን ለመቀነስ የሚያስችሉ ተግባራትን ማከናወን፤<br>➢ ለእንስሳት የግጦሽ ሣርን በአግባቡ መጠቀምና መጠበቅ፤ |

Ethiopian Meteorology Institute

ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ሠንጠረዥ 3 በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በዉሀዉ ዘር ላይ ሊኖር የሚችለው ተጽዕኖ

| ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|
| አባይ፣ ባሮ አኮቦ፣ ተከዜ በላኛዉና መካከለኛው ኦሞ ጊቤ፣ በላይኛዉ ስምጥ ሸለቆ፣ አዋሽ፣ | • የገፀ-ምድር ውሃ ፍሰት ማገገም<br>• የከርሰ-ምድር ውሃ ክምችት ማደግ<br>• የግድቦች የውሃ የማከማቸት አቅም መጎልበት<br>• የንጹህ መጠጥ ውሃ ተደራሽነት ማደ | • የደለል ክምችት ስጋት መጨመር<br>• የመንገዶች መጥለቀለቅና | • የዝናብ ውሃን አሰባስቦ ለተለያዩ አገልግሎቶች ማዋል<br>• የመጠጥ ውሃን አስተካክሎና አክሞ መጠቀም<br>• የውሃ ማፋሰሻና የመስመር ቦዮችን በጥንቃቄ ማፅዳት<br>• የጎርፍ አቅጣጫ ማስወገጃ መስመሮችን አስቀድሞ ማዘጋጀት |
| **ከቀላል እስከ መካከለኛ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት** | **አዎንታዊ ተጽዕኖ** | **አሉታዊ ተጽዕኖ** | **የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ** |
| የላይኛውና የመካከለኛው ገሊ ዳዋና ዋቢ ሸበሌ ተፋሰሶች | • የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት በመጠኑ መሻሻል<br>• የጎርፍ ሆነ የደለል ስጋት መቀነስ | • ከፍተኛ ትነት መኖር<br>• የአፈር እርጥበት መቀነስ | • የሚገኘውን የዝናብ ውኃ አክሞ መጠቀም<br>• ወራጅ የዝናብ ውኃን ማሰባሰብና ማጠራቀም<br>• ከቤት ጣራ ላይ ውኃ የማሰባባሰብ ማጠራቀም<br>የአየር ሁኔታ መረጃን በቅርበት መከላከል |
| **ደረቅ የአየር ሁኔታ** | **አዎንታዊ ተጽዕኖ** | **አሉታዊ ተጽዕኖ** | **የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ** |
| አፋር ደናክል፣ መረብ ጋሽ፣ ኦጋዴን፣ አይሻ፣ ታችኛው ስምጥ ሸለቆ፣ ገናሌ ዳዋ፣ ዋቤ ሸበሌ ተፋሰሶች | • የጎርፍ ሆነ የደለል ስጋት አለመኖር፣ | • የገጸ ምድር ትነት መጠን መጨመር | • የገጸ ምድር የውኃ ሀብትን በአግባቡ መጠቀም |